**ፕሬስ ሪሊዝ**

**ህዳር 25 ቀን 2000 ዓ.ም.**

**ማስታወቂያ ሚኒስቴር**

## <u>የአገሪቱን የልማት ዕድገት ቀጣይነት ለማረጋገጥ</u>
## <u>ፀረ-ሙስና ትግሉ ተጠናክሮ መካሄድ ይኖርበታል</u>

የተባበሩት መንግሥታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን ለመጀመሪያ ጊዜ ለፊርማ የቀረበበት ዕለት የፀረ-ሙስና ቀን ሆኖ እንዲከበር በተወሰነው መሠረት የዘንድሮው ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለአራተኛ ጊዜ በአገራችን ደግሞ ለሦስተኛ ጊዜ ህዳር 29 ቀን ይከበራል፡፡

ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ. በ2003 ኮንቬንሽኑን በወቅቱ የፈረመች ሲሆን ከቅርብ ወራት በፊት ደግሞ የተባበሩት መንግሥታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽንና የአፍሪካ ህብረት የሙስና መከላከያ እና መዋጊያ ኮንቬንሽኖችንም ከመፈረም ባሻገር ስምምነቶቹን አፅድቃለች፡፡

ሃገራችን የዘንድሮውን ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀንን ስታከብር እነዚህን ሁለት ስምምነቶች በማፅደቅ ለዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ትግል ያላትን ቁርጠኝነት በተግባር ያሳየችበት በመሆኑ የተለየ ቦታ ትሰጠዋለች፡፡ በዓሉ ድህነትን አሽቀንጥረን ለመጣል ቃል በመግባት አዲሱን ሚሌኒየም የተቀበልንበት እንዲሁም አገራችን በልማቱ መስክ ፈጣን ዕድገት ባስመዘገበችበት ዋዜማ የሚከበር በመሆኑ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡

የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ባለፉት 6 ዓመታት የሥነ ምግባር ትምህርትን በማስፋፋትና በማስረጽ ረገድ ባደረገው ጥረት ሙስና የመነጋገሪያ አጀንዳና ትኩረት የሳበ ጉዳይ ለመሆን በቅቷል፡፡ ከዚህ አኳያ የህብረተሰቡ የግንዛቤ ደረጃ የላቀ እንዲሆንና ተግባራዊ ምላሹም እንዲጐለብት ማድረግ ቀጣዩ የኮሚሽኑ ተግባር ይሆናል፡፡

ህብረተሰቡ ከኮሚሽኑ ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠሩም ጥቆማዎችን በመስጠት፣ ለምርመራ ሥራ የሚውሉ ልዩ ልዩ ዶክሜንቶችን እና ማስረጃዎችን በማቀበል፣ ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ሥር በማዋል፣ በምስክርነት በመቆም፣ በሙስና መከላከልና በትምህርት እንቅስቃሴዎች ውስጥ በመሳተፍ ድጋፉን ከጊዜ ወደ ጊዜ በማጠናከር ላይ መገኘቱ ኮሚሽኑ በመንግሥት የተሰጠውን ተግባር አጐልብቶ እንዲቀጥል አስችሎታል፡፡

ኮሚሽኑ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስከአሁን ወደ 9,000 የሚሆኑ ጥቆማዎችን ከህብረተሰቡ በመቀበል የተለያዩ ውሳኔዎችን የሰጠ ሲሆን የፍርድ ቤት ውሳኔዎችንም በተመለከተ 168 በሚሆኑ የሙስና ወንጀል ፈፃሚዎች ላይ በአመዛኙ ከ3 እስከ 19 ዓመት እሥራት እና ከ500 እስከ 20,000 ብር የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት እንዲወሰን አድርጓል፡፡ የሙስና ወንጀልን በመጠቀማቸው እና በመዋጋታቸው የተለያየ ጥቃት ለደረሰባቸው 40 ለሚጠጉ ዜጐችም ኮሚሽኑ ከለላ ሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም የሙስና ወንጀል ጠቋሚዎችና ምስክሮች ከለላ አዋጅ በዚህ ዓመት በተወካዮች ምክር ቤት ይፀድቃል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ይህም ኮሚሽኑ በተወሰነ መልኩ ለሙስና ወንጀል ጠቋሚዎች እና ምስክሮች ይሰጠው የነበረውን ከለላ በተጠናከረ መልክ ለማከናወን እንደሚረዳው ይታመናል፡፡

ኮሚሽኑ የፀረ-ሙስና ትግሉን ብቻውን ሊወጣው ይችላል ተብሎ ስለማይታሰብ አጠቃላዩን ህብረተሰብ በፀረ-ሙስና ትግሉ የማሰለፍ ተልዕኮ የተሰጠው የሥነ ምግባር አውታሮች ማስተባበሪያ መምሪያ ተደራጅቷል፡፡ መምሪያው ኮሚሽኑ ከሃይማኖት ተቋማት፣ ከሙያና ከብዙሃን ማኀበራት፣ ከመገናኛ ብዙሃን፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ከፍትህ አካላት እና ከመሳሰሉት ጋር በትብብር ለመሥራት የሚያስችለውን አቅም እንደሚፈጥርለት ይታመናል፡፡

ይኸው በዓል ሙስና የልማታችን እና የዕድገታችን እንቅፋት እንዳይሆን በአዲሱ ሚሌኒየም ከሙስና የፀዳች ኢትዮጵያን በጋራ ጥረት የምንገነባበትን ራዕይ ይዘን የምናከብረው ጭምር ነው፡፡

# # # #